መልእክት አሥራ ሁለት

**ራሱን የሚሰውር አምላክ—ስውሩ አምላክ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ኢሳ. 45፡15፤
ኤፌ. 3፡16-17፤ ፊልጵ. 2፡13፤ ሉቃ. 18፡1-8

**I. “የእስራኤል አምላክ መድኃኒት ሆይ፣ በእውነት አንተ ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ”—ኢሳ. 45፡15፡-**

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ራሱን እንደሚሰውር አምላክ እንደሚናገር የእግዚአብሔር ልጆች አያውቁም—ቁ. 15፡-

1. እግዚአብሔር ራሱን የሚሰውረው አምላክ ስለመሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች በቂ እውቀት እንደሌላቸው ይህ ያረጋግጣል።
2. እግዚአብሔርን እንደ ሁሉን ቻዩ አምላክ፣ እንደ ጻድቁ አምላክ እና በጸጋና በቸርነት እንደተሞላው አምላክ ልናውቀው እንችላለን፤ ነገር ግን ራሱን እንደሚሰውረው አምላክ እግዚአብሔርን ላናውቀው እንችላለን—ሉቃ. 1፡49፤ 1 ጴጥ. 5፡6፤ ራእ. 15፡3፤ ኤፌ. 2፡7፤ መዝ. 17፡7።

ለ. ምንም እንኳን አምላካችን በሁሉም ቦታ የሚገኝ፣ ሁሉን ቻይና በይቅር ባይነት የተሞላ ቢሆንም የአስቴር መጽሐፍ እንደሚያመለክተው እርሱ የሚሰወረው አምላክም ነው—4፡14።

ሐ. እግዚአብሔር አጽናፍ ዓለምን ፈጠረ ከዚያም እርሱን የት እንደምናገኘው እስከማናውቅ ድረስ ራሱን በአጽናፍ ዓለም ውስጥ ሰወረ—ኢዮብ 23፡3።

መ. እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች መካከል የማይቆጠሩ ነገሮችን አድርጓል፣ በግል ሕይወታቸውም የማይቆጠሩ ነገሮችን አድርጓል፣ ሆኖም ግን ራሱን ሰውሯል፤ ያለማቋረጥ ይሠራ ነበር፣ ሁልጊዜም ግን ስውር ነበር—ኢሳ. 45፡15።

ሠ. የምናገለግለው ሁሉን ቻዩ አምላክ አሁንም ሳይቀር፣ በተለይ ደግሞ ሲረዳን ሳለ፣ ራሱን እየሰወረ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል—ዮሐ. 14፡26፤ ሮሜ 8፡28፡-

1. እርሱን ማየት አንችልም፣ ምንም ነገር እያደረገ ያለም አይመስልም።
2. በእርግጥ ክርስቶስ በልባችን ቤቱን እንዲሠራ በመንፈሱ ወደ ውስጥ ሰውነታችን በኃይል ሲያጠነክረን ሳለ ስውር በሆነ መንገድ ለእኛ ብዙ ነገሮችን እያደረገ ነው—ቁ. 28፣ 34፤ አስቴ. 4፡14፤ ፊልጵ. 2፡13፤ ኤፌ. 3፡16-17።

ረ. ራሱን የሚሰውረው አምላክ በጸጥታ፣ ነገር ግን በኃይል በውስጣችን እየሠራ ነው—ፊልጵ. 2፡13፡-

1. ኃላፊነታችን በውስጣችን ጥልቀት ላለው ውስጣዊ ስሜት ምላሽ በመስጠት ከእርሱ ጋር መተባበር ነው—ሮሜ 8፡6።
2. እግዚአብሔር በውስጣችን እየኖረና እየሠራ እንደሆነ በተሰማን ጊዜ ሁሉ፣ አሜን ማለት አለብን፣ ምክንያቱም በውስጣችን ጥልቀት፣ በዚያ፣ በምሥጢርና ባለማቋረጥ ራሱን የሚሰውረው አምላክ እየሠራ ነውና።

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ካጠናን እግዚአብሔር ታይታን የሚጠላ ባሕርይ እንዳለው እናያለን፤ በግልጽ ከመሥራት ይልቅ በስውር መሥራትን ይወዳል—ማቴ. 6፡1-8።

ረ. የእኛ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ራሱን ከሚሰውረው ከእግዚአብሔር ባሕርይ ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ ነው—ኢሳ. 45፡15፡-

1. እግዚአብሔር መሰወርን ይወዳል፤ እኛ ታይታን እንወዳለን—ማቴ. 6፡1።
2. እግዚአብሔር ውጫዊ መገለጦችን አይናፍቅም፤ እኛ ደግሞ ያለእነርሱ አንረካም—ቁ. 2።
3. ይህ መለኮታዊ ባሕርይ ለእኛ ታላቅ መከራና ፈተና ነው።

**II. የአስቴር መጽሐፍ ራሱን የሚሰውረው የእስራኤል አምላክ በተበተኑ ጊዜ የተጨቆኑትን ምርጦቹን እንዴት በምሥጢር እንደ ተንከባከባቸውና በምርኮ የተሰደዱትን ምርጦቹን እንዴት በገሃድ እንዳዳናቸው ግልጽ የሆነ ዘገባ ይሰጠናል—1፡1-22፤ 2፡1-23፡-**

ሀ. የዚህ መጽሐፍ ዋና ነጥብ እስራኤልን፣ የአብርሃምን ዘሮች እንደ ምርጡ የመረጣቸው እግዚአብሔር ራሱ፣ ለአሕዛብ አገራት በምርኮኝነት ከሰጣቸው በኋላ በምሥጢር በመንቀሳቀስ እነርሱን በምሥጢር ለመንከባከብ እና በገሃድ ለማዳን ለእነርሱ ስውር አምላክ እንደሆነ ነው—ኢሳ. 45፡15፡-

1. የአስቴር መጽሐፍ የእግዚአብሔር ስም መጠቀስ በነበረበት ቦታ እንኳን ሳይቀር የእግዚአብሔርን ስም የማይጠቅስበት ምክንያቱ ይህ ነው— 4፡3፣ 16።
2. በአንድ በኩል፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመቅጣት የአሕዛብ አገራትን እንደ መሣሪያ ተጠቅሟል፤ በሌላ በኩል፣ ስውሩ አምላክ እየተንከባከባቸው ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ነበር።

ለ. ስውሩ አምላክ በምሥጢር ለእስራኤል ብዙ ነገሮችን አድርጓል፡-

1. ስውሩ አምላክ ከሕንድ እስከ ኢትዮጵያ በሚደርስ ታላቅ ግዛት ላይ በአሕዛብ ዓለም በሥልጣኑ የበላይ የሆነን ንጉሥ ሾመ—1፡1-2።
2. ስውሩ አምላክ፣ ንግሥቲቱ የበላይ የሆነውን የንጉሢን ቃል ባለመታዘዚ ምክንያት ንጉሡ ከሥልጣኗ እንዲያወርዳት አደረገ— ቁ. 3-22።
3. ምሥጢራዊ በሆነ እንክብካቤው ስውሩ አምላክ አስቴር የተባለችውን አይሁዳዊት ወላጅ አልባ ድንግል የበላይ በነበረው ንጉሥ ንግሥቲቱ ሆና እንድትሾም አስነሣት— 2፡1-18።

ሐ. በምርኮኝነት ዓመታት እግዚአብሔር ተሰውሮ ነበር፣ አሁንም ተሰውሯል፤ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ዘመን እንኳን እግዚአብሔር ራሱን እየሰወረ ነው—ኢሳ. 45፡15።

## III. በሉቃስ 18፡1-8 ያለው ምሳሌ ትርጉም ጥልቅ ነው፣ እኛም እግዚአብሔርን በዚህ ምሳሌ እንደተገለጠው፣ እንደ ስውሩ አምላክ ልናውቀው ያስፈልገናል፡-

ሀ. ቁጥር 3 ላይ ያለችው መበለት አማኞችን ታመለክታለች፤ በአንድ በኩል በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞች በዚህ ዘመን መበለት ናቸው፣ ምክንያቱም ባላቸው፣ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር ያለ አይመስልምና—2 ቆሮ. 11፡2።

ለ. በምሳሌው ላይ እንዳለችው መበለት (ሉቃ. 18፡3) እኛ በክርስቶስ የምናምን አማኞች እግዚአብሔር እንዲበቀልልን የሚያስፈልገን አንድ ጠላት፣ ሰይጣን ዲያቢሎስ አለ፡-

1. ይህ ምሳሌ ጌታ በግልጽ የማይገኝ በሚመስልበት ጊዜ ከባለጋራችን የሚደርስብንን መከራ ያመለክታል።
2. ጌታ በግልጽ የማይገኝ በሚመስልበት ጊዜ ባለጋራዋ ሁልጊዜ የሚያስቸግራት መበለት ነን።

ሐ. ባለጋራችን ሲያሳድደን ሳለ አምላካችን ጻድቅ አይመስልም፣ ምክንያቱም ልጆቹ ጻድቅ ባልሆነ መንገድ እንዲሰደዱ ይፈቅዳልና—1 ጴጥ. 2፡20፤ 3፡14፣ 17፤ 4፡13-16፣ 19፡-

1. በዘመናት ሁሉ በሺህ የሚቆጠሩ እውነተኛና ታማኝ የጌታ ኢየሱስ ተከታዮች በጽድቅ ያልሆነ ስደትን ተቀብለዋል፤ ዛሬም እንኳን ብዙዎች ጻድቅ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ እያለፉ ነው—ራእ. 2፡8-10።
2. አምላካችን ለመፍረድና ለመበቀል ስለማይመጣ ፍትሃዊ ያልሆነ ይመስላል፤ ከዚህ ሁኔታ የተነሣ ጌታ ኢየሱስ ለሚሰደዱት ሕዝቡ ምንም የሚያደርግ የማይመስለውን እግዚአብሔርን ለማመልከት ዓመፀኛ ዳኛን ተጠቀመ—ሉቃ. 18፡2-6።

መ. በምሳሌው ያለችው መበለት ከባለጋራዋ እንዲፈርድላት ወደ ዓመጸኛው ዳኛ መምጣቷን ቀጠለች፤ እንዲበቀልልን ጸንተን መጸለይ አለብን፣ መታከትም የለብንም—ቁ. 1፣ 3፡-

1. ባላችን ያለ በማይመስልበት ጊዜ እና እንደ መበለት በምድር ላይ ስንተው፣ ለጊዜው አምላካችን ዓመፀኛ ዳኛ የሆነ ይመስላል—ቁ. 6።
2. ምንም እንኳን ዓመፀኛ ቢመስልም፣ “ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ” ለምርጦቹ ፈጥኖ ስለሚፈርድላቸው ጸንተን በመጸለይ እርሱን መጨቅጨቅ አለብን—ቁ. 7-8።

ሠ. ራእይ 8፡5 ለ 6፡9-11 እና ለሉቃስ 18፡7-8 መልሱን ያመለክታል፡-

1. በራእይ 8፡3-4 ያለው የቅዱሳን ጸሎት የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ የሚቃወመው ምድር ላይ እንዲፈረድ መሆን አለበት።
2. በምድር ላይ የሚሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ—ምድር ላይ እሳት መጣሉ—በክርስቶስ እንደ ዕጣኑ የቅዱሳን ጸሎት መልስ ነው—ቁ. 3-5።

ረ. “የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?”—ሉቃ. 18፡8፡-

1. “እምነት” የሚለው የግሪኩ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም “ያን እምነት” ማለት ነው፤ ይህ ልክ እንደ መበለቲቱ ጸንተን እንጸልይ ዘንድ የጸናውን እምነት ያመለክታል።
2. የዳንበት እምነት የመጀመሪያው የእምነት ደረጃ ነው፤ ከክርስቶስ ጋር ወደ ሕይወት ጥምረት ያመጣን እምነት የሚያገናኘው እምነት—በእግዚአብሔር ልጅ እንኖር ዘንድ ሦስታንዱን አምላክ ባለማቋረጥ በመንካታችን በኩል ወደ ውስጣችን የሚመጣው እምነት—ነው—ሮሜ 1፡17፤ ገላ. 2፡20፤ ዮሐ. 14፡19።
3. የሚያገናኘው እምነት ክርስቶስ በድል ሲመለስ ድል ነሺዎቹ እርሱን ለመገናኘታቸው መለኮታዊው መሥፈርት ነው—ሉቃ. 18፡8፡-
   ሀ. የሚያገናኘው እምነት ፍለጋ ከሌለው ባለጠግነቱ ጋር እኛን ለማገናኘት ሦስታንዱ አምላክ በውስጣችን መንቀሳቀሱ ነው—ኤፌ. 3፡8።

ለ. የሚያገናኘው እምነት በራሳቸው ምንም መታመን የሌላቸው አማኞች እምነት ነው፤ ይልቁንም የሚታመኑት በእግዚአብሔር ነው—2 ቆሮ. 1፥9።

ሐ. ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ በሚያገናኘው እምነት እየኖሩ ያሉ በርካታ ድል ነሺዎችን ያገኛል፣ በሺህ ዓመት መንገሡም ለመንግሥቱ ውድ መዝገቦች አድርጎ ይቆጥራቸዋል—ሉቃ. 18፥8፤ ራእ. 20፥4፣ 6።

© 2022 Living Stream Ministry